በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መጋቢት 28 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 67ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው እለት ባካሄደው 67ኛ መደበኛ ስብሰባ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የጦር መሳሪያ ቁጥጥር የሀገርንና የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም የዜጎችን እና የህዝቦችን መብትና ደህንነት ለማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤ ግለሰቦች የታጠቋቸውን የጦር መሳሪያዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ጸጥታ ለማስጠበቅ ተግባር ሊውሉ የሚችሉበትን እድል መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በስራ ላይ ባሉ ህጎችና አሰራሮች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ህግ መደንገግ እና ወጥነት ያለው ስርዓት መፍጠር በማስፈለጉ እንዲሁም ሀገራችን ያጸደቀቻቸውን ህገወጥ የጦር መሳሪያ ቁጥጥርን የሚመለከቱ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈጸምና አለም አቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ እንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲላለፍ ወስኗል፡፡

//